# የታዋቂው ኣርቲስት ሰሎሞን ተካልኝ 12 ኛው ዓመት የትግራይ ፌስቲቫል ምክንያት በማድረግ ያስተላለፈው የድጋፍ መልእክትና መልካም አርአያነት

በውጭ ሃገር ለምትገኙና በየትኛውም ክፍለ ዓለም ለምትገኙ የትግራይ ብሄረሰብ ተወላጆች ኣባቶቼ፣ እናቶቼ፣ ወንድሞቼና እህቶቼ በቅድሚያ በዚህ ታሪካዊ ቀን በሰሜን ኣሜሪካ የትግራይ ብሄረሰብ ኣባላት (ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ) የእግር ኳስ ውድድር መዝጊያ ስነ ስርዓት ላይ ተገኝቼ የኪነ ጥበብ ሞያየን እንዳሳይ ስለተሰጠኝ ዕድል የተሰማኝን ከፍተኛ ደስታ እና የኢትዮጵያዊነት ስሜት ለመግለፅ ቃላቶች ያጥሩኛል፡፡

ወገኖቼ ፖለቲካ በጭፍን ጥላቻ እና ጭብጥ ኣልባ ወሬ ሲሞላ የሚያመጣውን ጉዳት ለእናንተ መናገር ለቀባሪው የማርዳት ያህል ነው፡፡ በተለይም እኔ የዚህ ዓይነቱ ፖለቲካ ሂደት ሰለባ የመሆኔን ያህል በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ለተሰሩ ጥፋቶች ሙሉ ሃላፊነት ለመውሰድ ድፍረቱም ሆነ ቀናነቱ እንዳለኝ ሳረጋግጥላችሁ ከፍተኛ ኩራት ይሰማኛል፡፡ በዚህ ኣጋጣሚ ባለይ ጥፋቶች ስሜታችሁን ለጎዳው ወገኖቼ ባደባባይ ይቅርታ የምጠይቅበት ከፍተኛ ኣጋጣሚ ተፈጥሮልኛል፡፡ ወገኖቼ ያለፈውን ጥለን ለወፊት ልንገነባው ላሰብነው የጋራ ሃገራችን የፍትህ፣ የእኩልነትና መልካም አስተዳደር ግንባታ እጅ ለእጅ ተያይዘን በጋራ እንደምንጓዝ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡

የትግራይ ህዝብ የሃገራችንን አንድነትና ሉአላዊነት በማስከበር ትግል ታሪክ ውስጥ በጀግንነት የተሞላ ገድል በደም የፃፈ ህዝብ ነው፡፡

ይሂንን ጀግና ህዝብ ጥሎ ወይም ወደ ጎን ገፍቶ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት፣ ስለ ህዝቦቿ መብትና ነፃነት ከቶም ማውሳት አይቻልም፡፡በመጨረሻም ከናንተ ጋር በቅርብ በጋራ ሃገራዊ ጉዳይ ላይ ማለትም በጦርነትም ሆነ በሰላም በመልካም አስተዳደርም ሆነ በዴሞክራሲያዊ ግንባታ በሞያየ ከጎናችሁ እንደምሰለፍ ሳረጋግጥ ፍፁም በሆነ ኢትዮጵያዊ ስሜት ነው፡፡ ሃገራችን ኢትዮጵያ በብሄር ብሄረሰብ ህዝቦቿ የጋራ ትግል በመፈቃቀድና በመከባበር ላይ ለተመሰረተው ሪፖብሊካችን ያለኝን ፍፁም የሆነ ታማኝነት እያረጋገጥኩ መጪው ዘመን ከበሽታ፣ ከችግር፣ ከኋላ ቀርነት የምንወጣበት ሰላምና ፍቅር የሚነግስበት እንዲሆንላችሁ ያለኝን መልካም ምኞት እየገለፅኩ ለሰጣችሁኝ እድል እና ወገናዊ የይቅር ባይነት ስሜት ከልብ አመሰግናለሁ፡፡